# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ታህሳስ 6 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የወለኔ ህዝብ የማንነት ጥያቄ በማንሳቱ ከወያኔ ጋር ግጭት ተቀሰቀሰ፤**

**በተቃውሞው ላይ የነበሩ አንድ አባት ተገደሉ ለ24 ሰዓት አስከሬናቸው በፌዴራል ፖሊስ ተከብቦ እንዳይነሳ ተደረገ፤**

**ሙስሊሙ ቀጣይ የአካባቢ ምርጫ ላይ አንሳተፍም አለ፤**

**በሽብርተኝነት ስም የታሰሩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህርና የመድረክ ስራ አስፈጻሚ ፅኑ እስራት ተፈረደባቸው፤**

**ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የተዘጋ ፋይል ተከፍቶበት በ50 ሺህ ብር ዋስትና ተለቀቀ፤**

በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን ውስጥ የሚገኙት የወለኔ ህዝብ የማንነት ጥያቄ በመንሳቱ ብቻ በወያኔ የፌዴራል ፖሊስ በተወሰደ እርምጃ አንድ ሰው ሲሞት ሌሎች በርካታ ሰዎች መቁሰላቸው ታወቀ::

ሰኞ ታህሳስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታ ወረዳ ልዩ ስምዋ ቤየር ተብላ በምትጠራው ከተማ የወረዳው ነዋሪዎች ከጉራጌ ተነጥለን እራሳችንን ችለን እንደ አንድ ብሔር እንወከል በሚል የሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ላይ ባሉበት ወቅት ድንገት የፌዴራል ፖሊስ በመድረስ ያለ አንዳች ማስጠንቀቂያ በከፈተው ተኩስ አንድ አባት ወዲያው ሲገደሉ ሌሎች ቁጥራቸው የበዛ ነዋሪዎች ክፉኛ ቆስለው በአቅራቢያቸው በሚገኙ የህክምና ማዕከል መወሰዳቸው ታውቆዋል::

ቁጥራችንም ሆነ የመኖሪያ የቆዳ ስፋታችን ከሌሎች የሀገሪቱ አናሳ ብሔሮች የተሻለ በመሆኑ ወለኔ እራሱን ችሎ ብሔር እንዲሆን ብለው ጥያቄ በማቅረባቸው ብቻ የተበሳጨት እነ ሬድዋን ሁሴን

በጉራጌ  ስር የምትጠቃለሉ እንጂ እራሳችሁን ችላችሁ አትጠሩም በማለት ምላሽ በመስጠታቸው የወለኔ ህዝብ በወረዳው ዋና ከተማ የሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ተቃውሞዋቸውን በማሰማት ላይ እያሉ ሳይታሰብ የፌዴራል ፖሊስ በወሰደው ድንገተኛ ጥቃት አንድ አባት የተገደሉ መሆኑ ታውቆዋል።

የአከባቢው ነዋሪዎች በወቅቱ የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዘው የፌዴራል ፖሊሶቹን ቢማጸኑዋቸውም ቁም ነገር ሳይሉዋቸው የተኩስ እሩምታ ከመክፈታቸውም በተጨማሪ በዱላ እና በሰደፍ የአካባቢውን ህዝብ እጅግ አሰቃቂ በሆነ መልኩ እንደደበደቡዋቸው ከስፍራው ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

የወለኔ ህዝቦች የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ ደም የጠማቸው የወያኔ ባለስልጣናት አግባብ ያለው ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ራሽያ ሰራሽ በሆኑ የጦር መሳሪያዎች የሰውን ልጅ ዘግናኝ በሆነ መልኩ ማስጨፍጨፋቸው አሳፋሪ ነው ያለው የወለኔ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት በዕለቱ ግድያ የተፈጸመባቸው አባት በጥይት መሆኑ እየታወቀና እየታየ በሌላ ችግር እንደ ሞቱ ለማስመሰል አስከሬናቸው ወደ አዲስ አበበ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል እንዲገባ መደረጉ ሌላው የወያኔ ድራማ ነው ብሎዋል።

ሰኞ ታህሳስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ተገድለው ለ24 ሰዓት አስከሬናቸው በፌዴራል ፖሊስ ተከብቦ እንዳይነሳ ተደርጎ እና ለቤተሰቦቻቸው ሳይሰጥ ከሁለት ቀን በሁዋላ ታህሳስ 3 ቀን 2005 ዓ.ም ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ወደ አዲስ አበባ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል እንዲመጣ ተደርጎ በዚያው ዕለት ሌሊት ምርመራው ተጠናቅቆዋል ተብሎ አስከሬኑ ወደ መኖሪያ ቀዬአቸው ተመልሶ ሐሙስ ታህሳስ 4 ቀን 2005 ዓ.ም በብዙ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ በተገኝበት ቀብራቸው መፈጸሙ ታውቆዋል።

የወያኔ ቡድን ቀን በጠራራ ጸሀይ የፈጸመው ግድያ መሆኑ እየታወቀና እየተረጋገጠ ለማስመሰል እና መረጃ ለማጥፋት ሲል  አስከሬን ምርመራ በሚል ቤተሰቦቻቸውን ለወጪ እና ለእንግልት ከመዳረጉም በተጨማሪ ሆን ብሎ የፈጸመው በመሆኑ ህዝቡ በቀብሩ ስነስርዓት ላይ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ ቁጣውን ሲገልጽ እንደነበር ተጠቁሞዋል።

ወለኔዎች ካለፈው ዓመት ጀምሮ ጥያቄውን ሲያቀርቡ የነበረ ቢሆንም አድማጭ በማጣታቸው ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝ ብለው በህጋዊ መንገድ በመሰረቱት በወለኔ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት በኩል ከፍተኛ ዘመቻ በመጀመራቸው የድርጅቱን ሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር ለእስር ሲዳረጉ በፍርሀት ጥያቄያቸውን ያቆማሉ ተብሎ የነበረ ቢሆንም ህዝቡ ግን ትግሉን አስፋፍቶ በአደባባይ ለተቃውሞ እስከ መውጣት መድረሱንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

አሰቃቂ ድርጊት የተፈጸመባቸው የወለኔ ህዝቦች በማግስቱ የኀበዝ አለቃቸውን መርጠው እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንዳሉ የወያኔ የክልል እና የፌዴራል በለስልጣናት በአካባቢው የሚከበሩ ሽማግሌዎችን መርጠው ወደ ስፍራው በመላክ ችግሩን  በውይይት ለመፍታት እንደሚፈልጉ በመግለጻቸው ዓርብ ታህሳስ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የመጀመሪያ ድርድር መደረጉን የደረሰን ጥቆማ አስታውቆዋል።

በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የ34 ቀበሌ ነዋሪ የወለኔ ህዝቦች ተወካይ ሽማግሌዎች ተውጣጥተው የወያኔ የፌዴራል እና የክልል ባለስልጣናትን ያነጋገሩ ሲሆን በወቅቱ በመጀመሪያ ስለተፈጸመው ግድያ ይቅርታ ካልጠየቃችሁን አንደራደርም በማለት አቋዋም በመያዛቸው የወያኔ ባለስልጣናት ሳይወዱ በግድ ከመቀመጫቸው ተነስተው ይቅርታ መጠየቃቸውንም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

በሀገር ሽማግሌዎቹና በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የተጀመረው ድርድር ያለ ውጤት የተበተነ ሲሆን ባለስልጣናቱ ሆን ብለው ግዜ ለመግዛት ካልሆነ በስተቀር አጥጋቢ በሆነ መልኩ መልስ ለመስጠት እንደማይፈልጉ ከወዲሁ የታወቀ ነው ሲል ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል።

ሰኞ ታህሳስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም የተገደሉት አቶ አክመል ሀጂ ባለትዳር እና የአራት ልጆች አባት እንደነበሩ የገለጸው የደረሰን ጥቆማ በዕለቱ ከቆሰሉት እና ህክምና ሲደረግላቸው ከነበሩት መሀከልም ሌላ አንድ አዛውንት መሞታቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

የወለኔ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት በሚል ህጋዊ ፍቃድ አውጥተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩት እነዚሁ በጉራጌ ዞን የገደባኖ ጉታ ነዋሪዎች ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ግዜ ጥያቄውን አቅርበው ምላሽ በማጣታቸው ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት በተዘጋጁበት ወቅት የድርጅቱ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበርን በሽብርተኛነት ከስሰው በማእከላዊ እስር ቤት አጉረዋቸው እንደሚገኙም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

በተያያዘ ዜና ከአንድ ዓመት በፊት በአወሊያ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተነሳውን የመብት ጥያቄ ተከትሎ የተቀሰቀሰውን ተቃውሞ ለማክበር እና የተጎዱትን ለማስታወስ የሚረዳ ፕሮግራም በምስጢር እየተዘጋጀ መሆኑ ታወቀ።

የአወሊያ መንፈሳዊ ተማሪዎች ያነሱትን የመብት ጥያቄ ተከትሎ ሙስሊሙ ህዝብ በመጅሊሱ ላይ ያቀረበው ጥያቄ ከቀን ወደ ቀን እየሰፋና እየጠነከረ መጥቶ ከወያኔ ጋር ከፍተኛ ግጭትን የፈጠረ ሲሆን ጥያቄው የተነሳበትን አንደኛ ዓመት አስመልክቶ ደማቅ አከባበር ለማድረግ በተለያዩ ቦታዎች ዝግጅቱ ተጠናክሮ እንደቀጠለም ለማወቅ ተችሎዋል።

በዚሁ በያዝነው ሳምንት ውስጥ ያከበሩትና ወደፊትም በተከታታይ የሚያከብሩት የአንድ ዓመት የተቃውሞ መታሰቢያ የተለያዩ ይዘት ባላቸው መንገዶች እንደሚገለጹና እስከ አደባባይ መውጣት ድረስ የሚከናወኑ መሆናቸውንም በምስጢር እየተዘጋጁ ካሉት አስተባባሪዎች የሾለከው መረጃ ያመለክታል።

በለፈው አርብ ታህሳስ 5 ቀን 2005 ዓ..ም የሙስሊሙ ህብረተሰብ ድምጻችን ይሰማ- መብታችን ይከበር፤ሰላም አጣን በሀገራችን፤ ጥቂቶቸ አይደለንም የሚሉና መፈክሮችን በማንገብ በአዲስ አበባው አንዋር መስጊድ፤ በደሴ፤ በወልቂጤ፤ በሀረር እና በሌሎች ስፍራዎች የተቃውሞ ድምጹን ሲያሰማ እንደነበር ታውቋል። ዝርሩን ወደ ኋላ እናሰማለን።

በሌላ ዜና በውስጡ በፍርሀት እና እርስ በርስ በተፈጠረ ችግር ተወጥሮ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችን የተለያዩ ታፔላ እየለጠፈ ለእስር መዳረጉን አስፋፍቶ እንደቀጠለበት ሰሞኑን የወሰደው እርምጃ ያረጋገጠ መሆኑ ታወቀ::

ለኦሮሞ ህዝብ እንታገላለን ብለው በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ሰሞኑን በወሰደው እርምጃ ከ3 ዓመት እስከ 13 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ቅጣት ማስተላለፉን ተከትሎ በሀገሪቱ መነጋገሪያ ሆኖ ሰንብቶዋል::

በፍርሀት ውስጥ ተወጥሮ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ከአንድ ዓመት በፊት ከኦነግ ጋር በመተባበር...አባል በመሆን...አባል በመመልመል...በሽብር ተግባር ላይ ለመሳተፍ ሙከራ በማድረግ በሚሉ ሰንካላ ምክንያቶች ሲያንከራትታቸው ከርሞ ማክሰኞ ታህሳስ 2 ቀን 2005 ዓ.ም የእስራት ፍርድ መስጠቱ ታውቆዋል::

የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የመድረክ አባል ስራ አስፈጻሚ እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር በነበሩት በአቶ በቀለ ገርባ ላይ የ8 ዓመት ጽኑ እስራት ሲወስን በኦሮሞ ህዝብ ኮንግሬስ ስራ አስፈጻሚና አመራር በሆነው ኦልባና ሌሊሳ ላይም የ13 ዓመት ፅኑ እስራት መወሰኑ ታውቆዋል::

በተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች ተማሪዎችን በመቀስቀስ እና በአመጽ እንቅስቃሴ ላይ እንዲሳተፉ ከፍተኛ ስራ ሲሰሩ ነበር የተባሉ ሌሎች 7 ተከሳሾችም ላይ ተመሳሳይ የጽኑ እስራት እርምጃ እንደተወሰደባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ጥቅምት 22 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ ማክሰኞ ታሕሳስ 2 ቀን 2005 ዓ.ም የእስራት ቅጣት ውሳኔ ማስተላለፉ ታውቆዋል::

በዚህም መሰረት

1ኛ-በቀለ ገርባ በ8 ዓመት ፅኑ እስራት

2ኛ-ኦልባና ሌሊሳ በ13 ዓመት ፅኑ እስራት

3ኛ- ወልቤካ ስሜ በ7 ዓመት ፅኑ እስራት

4ኛ-አደም ሙሳ በ3 ዓመት ፅኑ እስራት

5ኛ-ወ/ት ሐዋ ዋቁ በ5 ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት

6ኛ-መሐመድ ሙሉ በ10 ዓመት ፅኑ እስራት

7ኛ-ደረጀ ከተማ          በ8 ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት

8ኛ-አዲሱ ሞክሬ          በ10 ዓመት ፅኑ እስራት

9ኛ-ገልገሎ ጎፋ          በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እና ለ4 ዓመት ከህዝባዊ መብቶቻቸው እንዲታገዱ ሲል ውሳኔ እንደተላለፈባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን እና አባሎች ላይ የወያኔ አገልጋይ የሆኑ ጭፍን ዳኞች ውሳኔ ከሰጡ በሁዋላ በመላ ሀገሪቱ የተለያዩ አስተያየቶች እየተሰነዘሩ ከመሆኑም ባሻገር ኦህዴድ የተባለው የህወሀት አቀንቃኝ ቆሜለታለሁ በሚለው ኦሮሞ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ደባና ተንኮል እየሰራ መሆኑን የተጋለጠበት ወቅት ነው ተብሎዋል::

አንድም ዜጋ ማስረጃ ሳይያዝበት በጸጥታ ኃይሎች አይያዝም..... አይታሰርም.....የሚለውን ወያኔ እራሱ ያወጣውን ህግ በመጣስ እና በመደምሰስ ሌላ ህግ በመፍጠር ያለ አንዳች ማስረጃ ሽብርተኛ ነው ከሚሉት የተቃዋሚ ፓርቲ ጋር አያይዘው ለእስር መዳረጋቸው የሚያሳፍር ከመሆኑም በላይ ወያኔ የውስጥ ችግሩን ሊያዳፍንበት እየሞከረ ነው ተብሎዋል::

ያለ አንዳች ምክንያት እና ማስረጃ ከያሉበት ተለቅመው ለእስር ተዳርገው ለረዥም ግዜ በማዕከላዊ ምርመራ ሲንገላቱ የቆዩት እነዚሁ የፖለቲካ እስረኞች በሁዋላም ወደ ቃሊቲ እንዲወርዱ ተደርገው ሲንገላቱ ከመቆየታቸውም በላይ በሚያሳዝን ሁኔታ ከ3 ዓመት እስከ 13 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት በመፈረዱ ቤተሰቦቻቸው በከፍተኛ ሀዘን ተውጠው እንደሚገኙ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልጹ ተደምጠዋል::

በእነ በቀለ ገርባ ላይ ምስክር ሆነው እንዲቀርቡ የተደረጉት ሰዎች የወያኔ አባሎች እና የጥቅም ተካፋዮች ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ታፍነው ለእስር ይዳረጉና የሚመሰክሩትን በግዳጅ አጥንተው ወደ ችሎት እንዲገቡ እንደተደረገ ምስክሮቹ በራሳቸው አንደበት ለህዝብ ሲገልጹ ተደምጠዋል::

የሚያሰዝነው እና የሚያሳፍረው ይላሉ በአሁኑ ሰዓት በሽብርተኝነት ተከስሰው በ8 ዓመት ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው የኦፌዴን ምክትል ሊቀመንበርና የመድረክ አመራሩ አቶ በቀለ ገርባ ባለቤት ወ/ሮ ሀና ረጋሳ በየዓመቱ ምስጉን መምህር እየተባለች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለረጅም ዓመታት ስትሰራ የነበረ ቢሆንም በቅርቡ ግን ባለቤትዋ ለእስር በተዳረገ ማግስት ጀምሮ ከቦታዋ አንስተው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንድታስተምር መደረግዋ አንዱ የወያኔ የስነ ልቦና መቅጫ ነው ሲሉ ታዛቢዎች ይናገራሉ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከ5 ወራት በፊት በወያኔ ቡድን ደህንነት እና ባለስልጣናት ተንኮል እና ትዕዛዝ ህትመቱ የተቋዋረጠው የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

ላይ ተቋዋርጦና ተዘግቶ የነበረው የፈጠራ ክስ እንደ አዲስ ተመስርቶ ማክሰኞ ታህሳስ 2 ቀን 2005 ዓ.ም ፍርድ ቤት መቅረቡ ታወቀ::

በጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ላይ የተመሰረተው ክስ ባለፈው ዓመት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በሞተበት ሰሞን ነሐሴ ወር ውስጥ ሲሆን በዚሁ ሳቢያ ያለ አንዳች ክርክር ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ተወርውሮ ለ7 ቀናት ታስሮ በሁዋላም በነጻ እንዲለቀቅ የተደረገ ቢሆንም ከ5 ወራት ቆይታ በሁዋላ መልሰው በአዲስ መልክ ክስ መስርተው ፍርድ ቤት ማቅረባቸው ታውቆዋል::

የተከሰሰበት እና ቃሊቲ እስር ቤት የታሰረበት ብሎም የተፈታበት ሁኔታ በግልፅ ሳይታወቅ በሰባት ቀናት ውስጥ በተሰራ ድራማ ሁሉም ተጠናቅቆ የነበረ ቢመስልም ከህትመት በተወገደችው ፍትሕ ጋዜጣ ምትክ አዲስ ታይምስ በሚል በየ15 ቀኑ የሚታተም መጽሔት በመጀመሩ የተበሳጩት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት እንደገና እንደ አዲስ ከ5 ወራት ቆይታ በሁዋላ ክስ መስርተው ፍርድ ቤት ማቅረባቸው አስገራሚ ድራማ ነው ሲሉ የህግ ባሙያዎች ሲገልጹ ተደምጠዋል::

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ በፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኖ በሰራበት ወቅት ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል እና በአመጽ እንዲፈርስ ብሎም ሕዝባዊ አመጽ እንዲቀሰቀስ በማሰብ በተለያዩ ግዜያት በፍትህ ጋዜጣ ላይ አሳትሞ ባሰራጨው የሀሰት ወሬ ክስ ተከስሶዋል በሚል ክስ ያቀረበበት ሲሆን የተመስገን ደሳለኝ ጠበቆች ክሱ ቢቀርብም ዋስትና የሚያስከለክል ባለመሆኑ ዋስትናው መብት ይከበር በማለታቸው በ50 ሺህ ብር ዋስትና እንዲለቀቅ መደረጉም ታውቆዋል::

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ በዕለቱ ችሎት በቀረበበት ወቅት በጠበቆቹ አማካኝነት ክሱን የተቃወመ ከመሆኑም በላይ ክሱ ተዘግቶዋል ተብሎ ከእስር የተለቀቀ መሆኑ እየታወቀ ዓቃቤ ህግ እንዳሻው እየፈነጨ እና እየተዝናና ባሻው ግዜ የዜጎችን ህይወት ምስቅልቅሉን በሚያወጣ መልኩ የፈጠራ ክስ እንደ አዲስ መጀመሩ የሀገሪቱን ህግ የሚጥስ በመሆኑ ውድቅ ይደረግ ብሎ የተከራከረ ቢሆንም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ የሆኑት  ዳኞች ክሱን ተቀብለው እንዲቀጥል ማድረጋቸው ታውቆዋል::

የተመስገን ደሳለኝ የክስ ሂደት ከመታየቱ በፊት 2ኛ ተከሳሽ የሆነው የፍትህ ጋዜጣ አሳታሚ ማስተዋል የህትመትና ማስታወቂያ ድርጅት ባለቤት ወይም ተወካይ እንዲቀርብና መልስ እንዲሰጥ ብሎ ዓቃቤ ህግ በጠየቀው መሰረት ዳኛውም ተስማምቶ ለታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱ ታውቆዋል::

በተመሳሳይ ዜና በሽብርተኝነት ተከስሳ በቃሊቲ እስር ቤት እየማቀቀች የምትገኘው ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ ማክሰኞ ታህሳስ 2 ቀን 2005 ዓ.ም ለሰበር ችሎት ያቀረበችውን የይግባኝ አቤቱታ ለማየት እና ውሳኔ ለመስጠት በተመሳሳይ ለታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም መቀጠሩ ታወቀ::

ለሽብርተኛ ድርጅት ተመልምላለች..... ከሽብርተኛ ጋር ትሰራለች...ለፀረ ሽብርተኛ መረጃ ታቀብላለች በሚል የሀሰተኛ እና የፈጠራ ክስ ተመስርቶባት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ14 ዓመት ፅኑ እስራት እና የ33 ሺህ ብር ቅጣት ተጥሎባት የነበረው ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ ለጠ ቅላይ ፍርድ ቤት

ባቀረበችው አቤቱታና ተቃውሞ ከቀረቡባት 4 ክሶች ሁለቱ ውድቅ በመደረጋቸው የ14 ዓመቱ ወደ 5 ዓመት እስራት ዝቅ ሲደረገላት የተጣለባት የብር ቅጣት ሙሉ ሙሉ መሻሩም ይታወቃል።

በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ አግባብ ያልሆነ ከመሆኑም በላይ መሰረታዊ የህግ ጥሰት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታይልኝ  በማለት ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበችው አቤቱታ ማክሰኞ ዕለት በጠበቃዋ አማካኝነት ቀርቦ የተደመጠ ሲሆን ጉዳዩን በጥልቀት ለመመርመር እና ለመመልከት በሚል ለታህሳስ 24 ቀን ከሰዓት በሁዋላ ቀጠሮ መሰጠቱ ታውቆዋል።